በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 10-12 የ8ኛ ክፍል የሁለተኛ መንፈቅ ዓመት የሞደል ፈተና 2016ዓ.ም የተሰጠ ሰዓት 1:00

መመሪያ አንድ ከተራቁጥር 1 - 22 የተሰጡ ጥያቄዎች ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ መስጫው ላይ አጥቁር/ሪ።

1. ወይዘሮ ሂሩት ገበያ ሄደው ብዙ ብር **<u>ፈጁ</u>** የተሠመረበት ቃል አውዲዊ ፍቺ_____ነው።

A. መደቡ C. ሸመቱ

B. አወጡ D. አገኙ

2. የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ይረብሻሉ እንዴ___ __በባዶው ቦታ የሚገባ ስርዓተ ነጥብ

A. ነጠላ ሰረዝ C. ጥያቄ ምልክት

B. ድርብ ሰረዝ D. አራት ነጥብ

3. ዋው ___ በጣም አምሮብሃል___ ባዶቦታውን የሚገባ ስርዓተ ነጥብ

A. ትምህርተ ጥቅስ C. ሁለት ነጥብ

B. ትምህርተ ስላቅ D. ቃላጋኖ

4. በልቦለድ ውስጥ የልቦለዱ ባለ ታርክ _____ ይባላል።

A. ገጸባህሪ C. ተራኪ

B. ደራሲ D. ታርክ

5. የሁላችንንም **<u>ቀልብ የሳበ</u>** ነገር ተከሰተ። ለተሰመረበት ሀረግ ተመሳሳይ ሊሆን የሚችለው ቃል የትኛው ነው?

A. የማረከ C. ያተኮረ

B. የጎተተ D. ያሰለቸ

6. ልጁ ምሳውን **<u>ይበላል</u>** ። የተሠመረበት ቃል እንዴት ይነበባል?

A. ጠብቆ C. ተለያይቶ

B. ላልቶ D. ተጣምሮ

7. የዶሮ አይን የመሰለ _____ እቤት አለ።

A. ውጥ C. ጠጅ

B. እንጀራ D. ጠላ

8. "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" የሚለው ተረትና ምሳሌ ለየትኛው ሐሳብ ማብራሪያ ይሆናል?

A. ለጦርነት C. ለአንድነት

B. ለፍቅር D. ለሀብት

9. **ደንብ** ለሚለው ቃል አውዳዊ ፍቺው_____ ነው ።

A. ህግ C. ስርዓት

B. ድንጋጌ D. ሁሉም

10. በአንድ ጽሑፍ ውስጥ የሚንፈልገውን አንኳር ሃሳብ በአፋጣኝ አንብበን ለማግኘት የሚንጠቀም የንባብ ዓይነት:-

A. የአሰሳ ንባብ C. የዝግታ ንባብ

B. የገረፍታ ንባብ D. ሰፊ ንባብ

11. ዝርዝር መረጃን ሳይሆን አጠቃላይ የጽሑፍን ሀሳብ ለመረዳት የሚጠቅመን የንባብ ዓይነት

A. የዝግታ ንባብ C. የገረፍታ ንባብ

B. የአሰሳ ንባብ D. ሰፊ ንባብ

12. የተፀው ስም የሆነው የቱ ነው ?

A. አዋሽ C. እንስሳ

B. ንፋስ D. አልጋ

13. የቁሳቁስ ስም ያልሆነው የቱ ነው ?

A. ወንበር C. እንስራ

B. አልጋ D. መኪና

14. የረቂቅ ስም መጠሪያ የሆነው የቱ ነው ?

A. መንፈስ C. ሀገር

B. ተራራ D. ፀሐይ

15. በግጥም ውስጥ አንድ ሃሳብ ላይ ትኩረት የሚያደርግ የስንኝ ስብስብ_____ ነው።

A. ሐረግ C. አንጓ

B. ቤት D. ቤት መምቻ

16. በአንድ ነገር መከሰት ምክንያት የሚመጡ ውጤቶችን ለማመልከት የሚረዱ አያያዥ

A. ውጤት አመልካች አያያዥ C. ተጨማሪ ሃሳብ አያያዥ

B. አማራጭ አያያዥ D. አፍራሽ ሀሳብ አያያዥ

17. ከቀረቡት ነገሮች አንዱን ለመውሰድ የሚንጠቀመው አያያዥ

A. ተጨማሪ ሀሳብ አያያዥ C. ተቃራኒ ሀሳብ አያያዥ

B. አማራጭ ሀሳብ አያያዥ D. ውጤት አመልካች አያያዥ

18. ገፀ ባህርይ በስንት ይከፈላል? A. 4 C

B. 2 C. 3 D. 5

19. የልቦለድ ታሪክ በመተረክ ላይ እያለ በመሃል እየገባ ወይም አየወጣ የምተውን

A. ደራሲ C. ዋና ገፀ- ባህርይ

B. ገፀ -ባህርይ D. ንዑስ ገፀ- ባህርይ

20.አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም የሆነ_____ነው።

A. እኛ C. እሱ

B. አንተ D. አንቺ

21. ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም

A. እናንተ C. እነሱ

B. አንተ D. እሱ

22. ግጥም በተመሳሳይ ሆሄያት ወይም ድምጾች ሲሰነኙ _____ ይባላሉ።

A. ቤት መታ C. ቤት መድፊያ

B. ቤት መምቻ D. አንጓ

መመሪያ ሁለት ከተራቁጥር 23 - 28 የተሰጡ ምሳሌያዊ ንግግሮች መልስ ልሆኑ የሚችሉትን መመምረጥ በተሰጠው መልስ መስጫ ላይ አጥቁሩ

23. ሀብት የጠዋት ጠዛ ነው።

A. ሀብት ብዙ ነው C. እጅግ ሀብታም

B. ሀብት ጠፊ ነው D. ምንም ሀብት የለሌው

24. ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

A. የሌለውን ያለበታ መፈለግ
C. ከአቅም በላይ መመኘት
B. ልማደኛ ልማዱን አይተውም
D. የተገላብጦሽ ተግባር ተፈፀመ

25. ሰው ማመን ቀብሮ ነው።

A. ሰው ታማኝ ነው
C. ሰው አይታመንም
B. ሰው ማመን መልካምነት ነው
D. ሰውን ለማመን መተዋወቅ ያስፈልጋል

26. ቀጥኜ ቢያዩኝ ጅማት ለመኑኝ።

A. አስቸገሩኝ
C. ክር ቸገራቸው
B. ክፉ አደረጉኝ
D. ናቁኝ

27. እንኪንስ እናቴ ሞታ እንዲሁም አልቅስ አልቅስ ይለኛል።

A. ከፍቶኛል
C. ለቅሶ አልወድም
B. ለቅሶ መሄድ እወዳለው
D. ደስተኛ ነኝ

28. የበላቤትን ወጪት ሰባሪ።

A. የማያፍር
C. ጥንቃቄ የሌለው
B. ውለታቢስ
D. የማይጠግብ

መመሪያ ሦስት ከተራቁጥ29 -35 ያሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ሙሉ የሚያደርጉ ትክክለኛ ሐረጎችን በመምረጥ መልስ መስጫ ላይ አጥቁር/ሪ።

29. ሞኝ ብያከብሩት _____

A. ያከብራል
C . የፈሩት ይመስለዋል
B. ይከራከራል
D. ያሳፍራል

30.አፍንጫ ብመቱት_____

A. ያለቅሳል
C. ያማል
B. ያቃጥላል
D. አይን ያለቅሳል

31. ጋኖች አለቁና _____

A. ምንቸቶች ጋን ሆኑ C. ተጣሉ

B . ሌሎች ጋኖች ተገዙ D. አገልጋዮች ጠፉ

32. ብርሌ ከነቃ _____

A. አይሸጥም C. ጠጅ አያስጠጣም

B. አይሆንም ዕቃ D. ጠጅ ያጣፍጣል

33. የፈሰሰ ውሃ_____

A. አይጠጣም C. አይታፈስም

B. ቆሻሻ ይሆናል D. መሬት ውስጥ ይሰምጣል

34. ጅብ ከሄዴ _____

A. ውሻ ሮጠ C. ሰላም ሆነ

B. ነጋ D. ውሻ ጮኸ

35.ትንሽ ስጋ _____

A.በመንጋጋ C. ከዘመድ ጋር

B. እንደ መርፌ ትዋጋ D. ቁርስ አይሆንም

መመሪያ አራት ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ በተሰጠው መልስ መስጫወረቀት ላይ አጥቁር /ሪ።

36. እግረ ደረቅ	A. እድለ ቢስ	B. እድለኛ	C. ቀጭን እግር	D. እግረ ብረት
37. ፈነጨ	A. ተናደደ	B. ተገረመ	C. ተደሰተ	D. ቀልጣፋ
38. መንጋ	A. ሰፈር	B. እንስሳት	C. የኋላ ጥርስ	D. ስብስብ
39. ለገሰ	A. መታ	B. ሰጠ	C. ከለከለ	D. ዳበረ
40. ላጤ	A. ያላገባ	B. ልጅ	C. ባለትዳር	D. ዘመድ
41. ሌት ተቀን	A. ቀንና ማታ	B. አልፎ አልፎ	C. ሁል ግዜ	D. አንዳድ ቀን
42. መግራት	A. መሰልጠን	B. መምራት	C. መግረፍ	D. መታገል
43. ቁንን	A. ዝምተኛ	B. ኪሩ	C. አጭር	D. ድንክዬ

44. ፋይዳ A. ምትክክ B. ምኞት C. ገድል D. ጥቅም

45. ገድል A. ታርክ B. ልምድ C. ምስጢር D. መጽሐፍ

መመሪያ አምስት ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎችበምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ መስጫ ወረቀት ላይ አጥቁር /ሪ።

ምንባብ

አንድት ወፍ በበረሃ ሰማይ ላይ ስትበር ብዙ ጊዜ ከመቆየቷ የተነሳ ውሃ ጠማት። ውሃ ለመጠጣት ስትፈልግ አንድ የውሃ እንስራ አየች። ወደ ውሃ እንስራ ተጠግታ ስትመለከት ውሃው ጎዶሎ ስለነበረ ለመጠጣት እንደምትችገር ተገነዘበች። ከዚያም ውሃ የያዘውን እንስራ በድንጋይ ለመስበር ብትሞክርም አልተሳካላትም። ጥቂት ካሰበች በኃላ ትናንሽ ጠጠሮችን እየለቀመች ወደ ውሃው እንስራ ውስጥ መጨመር ጀመረች ። ቀስ በቀስ ውሃው ወደ እንስራው አፍ እየተጠጋ መጣ። ከዚያም ጠጥታ ጥሟን አረካች ።

46. ከተሰጡት አማራጭ ውስጥ የምንባቡ ርዕስ መሆን የምችል የቱ ነው?

A. የውሃ እንስራ C. ብልጧ ወፍ

B. የተጠማች ወፍ D. ጎዶሎ እንስራ

47. ወፊቷ ውሃውን ለመጠጣት ያስችገራት ነገር ምን ነበር ?

A. ሰማይ ላይ መሆኗ C. እንስራው ከመጠን በላይ መሙላቱ

B. እንስረው ጎዶሎ መሆኑ D. እንስራው በመከደኑ

48. ወፏ ውሃውን ለመጠጣት ሞክራ ያቃታት ዘዴ የቱ ነው ?

A. እንስራውን በድጋይ መስበር C. እንስራው ውስጥ መግባት

B. እንስራው ውስጥ ጠጠር መሙላት D. የእንስራውን ክዳን መክፈት

49. ወፊቷ ውሃ ለብዙ ጊዜ ሳትጠጣ የቆየችው የት ነገር ?

A. እንስራው ላይ C. ዋሻ ውስጥ

B. ዛፍ ላይ D. በረሃ ሠማይ ላይ

50. በመጨረሻ ግዜ ውሃውን ለመጠጣት ወፏ የተጠቀመችው አማራጭ መንገድ የቱ ነው ?

A. እንስራውን መስበር C. ወደ ወንዝ መሄድ

B. እንስራው ውስጥ ጠጠር መጨመር D. የሰዎችን እርዳታ መጠየቅ

መመሪያ ስድስት ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተቃራኒ ፍቻቸውን በመምረጥ በተሰጠው መልስ መስጫወረቀት ላይ አጥቁር /ሪ።

51. ሙገሳ	A. አድናቆት	B. ስድብ	C. መለማመጥ	D. ማክበር
52. በጠሰ	A. ቀጠለ	B. ቆረጠ	C. ቆራረጠ	D. አሸነፈ
53. አከበረ	A. አሞገሰ	B. ወደደ	C. አዋረደ	D. እጅ ነሳ
54. ወለል	A. ሰፊ	B. ቤት	C. ጣሪያ	D. ግልጽ
55. አመነ	A. ተስፋ አደረገ	B. እራሱን ሰጠ	C. ከዳ	D. ተማመነ
56. ጫጨ	A. ፋፋ	B. ከሳ	C. ሰውነቱ አለቀ	D. ቀጨጨ
57. ሀሩር	A. ቆላ	B. ሙቀት	C. ቁር	D. ብርድ
58. ቅጣት	A. ውርደት	B. ክብር	C. ፍርሃት	D. ሽልማት
59. ተናደ	A. ተገነባ	B. ፈረሰ	C. አማረ	D. ተጀመረ
60. ህይወት	A. ሞት	B. እስትንፋስ	C. መኖር	D. ደስታ